# አሚክሮን፡ እኛ የምናውቀው

## አሚክሮን ቫርያንት ምንድን ነው?

ልክ እንደ ኮቪድ-19 መንስኤ የሆኑ ቫይረሶች ሁሌም ይለወጣሉ። ይህ ትልቅ የ ቫይረስ ለውጥ ቫርያንት ይባላል። አንዳንድ ቫርያንቶች የበለጠ አደገኛ እና/ ወይም በቀላሉ ሊሠራጩ ይችላሉ። ኦምክሮን በቀላሉ የሚሠራጭ ቫርያንት ነው።

## እራስዎን እና ቤተሰብዎን እንዴት መጠበቅ ይችላሉ?

እራስዎን ፣ቤተሰብዎን እና ማህበረሰቡን ከ ኮቪድ-19 ለመከላከል ምርጡ መንገድ ጭምብል በመልበስ እና ከ 5 ዓመት በላይ የ ሆኑ ሁሉም የቤተሰብዎ አባላት በተቻለመጠን ሙሉ በሙሉ እንዲከተቡ ማድረግ ነዉ። ያልተከተቡ ሠዎች በቫርያንት የመበከል፣በጠና የመታመም እና ወደ ሌሎች የማሠራጨት ዕድላቸዉ ከፍተኛ ነው።

## ስለ ቡስተርስ?

የ ሳይንስ ሊቃዉንቶች አንዳንድ ክትባቶች የ አንድ ሠዉ የመከላከል/የመጠበቅ አቅሙ ከ ግዜ ወደ ግዜ እየቀነሰ መምጣቱን ደርሰዉበታል እናም ቡስተር ክትባት ተከላክሎ ለማቆየት ይረዳል። በተጨማሪም ኮቪድ-19 ቡስተር እርሶን ከ አዳዲስ ቫርያንት ለመከላከል ሊረዳ ይችላል።
የሚከተለዉ ሲሆን ቡስተር ማግኘት ይኖርቦታል፡

. የ ሁለተኛውን ዙር ክትባት ከወሰዱ ከ አምስት ወራት በላይ(ሞደርና እና ፋይዘር)
. የ ጆንሰን እና ጆንሰን ክትባት ከወሰዱ ከሁለት ወራት በኃላ
. በሌላ ሀገር ከወሰዱት የመጨረሻ የክትባት መጠን ከ አምስት ወራት በላይ

የራስዎን እና የሌሎችን ደህንነት ለመጠበቅ ተጨማሪ መንገዶች፡

- ጭምብል ማድረግ
- አካላዊ እና ማህበራዊ ርቀትን መተግበር
- ትልቅ መሰብሰብን ማስወገድ
- እጆችዎን በተደጋጋሚ መታጠብ
- በሕመም ግዜ ቤት ዉስጥ መቆየት
- ምልክቶች ከታዩ ወድያዉኑ የኮቪድ-19 ምርመራ ማድረግ